# አንተ ጋዜጠኛ

የሀገር መሪነት በእድል ተወስኖ
ሰብሳቢ በማጣት ህዝብህ ተበትኖ
ማየት የደከመህ የሀገር ሀብት ባክኖ
በጥቂት ቂመኞች ስልጣኑ ተወርሮ
ነፃነት አንድነት ሰውነት ተሽሮ
ታሪክ ያቆየልህ አንድነት ተቀብሮ
በሰውነት ኮርቶ በአገሩ ተከብሮ
መኖርን ተነፍጎ በበደል ተመርሮ
ጥገኝነት መርጦ በአሜሪካ ሰፍሮ።
ያገር ወገን ፍቅር ጭራሽ ሳይለው
ለጥቅሙ ተገዝቶ መኖር ሳይታየው
የጭቁኑ ዜጋው መብከን ያሰቃየው
በነፃነት ፍቅር መንፈሱ የጋየው።
በሰፊው ህዝብ አምነህ ሳትሆን ጎሰኛ
የወገንህ ስቃይ ብሎህ አላስተኛ
ለሰላም የቆምከው ፍጹም እውነተኛ
ለነፃነት ታጋይ አንተ ጋዜጠኛ።
በአገርህ ተጓድሎ ዳኝነትም ፍርድ
በወገንህ ስቃይ ስትጨስ ስትነድ
ሰሚ በማጣትህ ስትጽፍ ስትቀድ
አገር የለቀቅከው ሆኖብህ የግድ።
በአስከፊ ስርአት ህዝብን አደንቁሮ
ለእውነት የቆመውን እጅና እግር አስሮ
በግፍ ባከማቸው ብር አእምሮው ዞሮ
ለአለም ህዝብ ሊያሰማ የረሀብ እሮሮ
በኢትዮጲያ ሊዶልት ከመሪ ጋር አብሮ።
የአለም መሪዎች ሊሰሩ ቁም ነገር
ጠረጴዛ ከበው ተቀምጠው ከወንበር
ሁሉም በየተራው ተነስቶ ሲናገር።
ሁሌ የሚጓዘው ጊዜ ተሽከርክሮ
ሰው የማይወስነው ሆነና ቀጠሮ
አንደኛው ተጋብዞ በስራው ተከብሮ
በእውነት ተሞልቶ በህግ ተወጥሮ
ቆሞ ሲመለከት ሁሉንም በአንክሮ
መድረክ ተደላድሎ ደቂቃው ተቋጥሮ
ከአገር ህዝብ በዳዩ ሲያገናኘው አብሮ
ጠመንጃ አንጋቹ ጀግናውን ጠርጥሮ።
ጌታው መናገሪያው ጊዜው ስለመጣ
በጥይት ተማምኖ ተሞልቶ በቁጣ

አገር በለመደው ነፃነት እረገጣ
በሞት አስፈራርቶ በቶሎ እንዲወጣ
ጠመንጃ ጨብጦ ወደእሱ ቢመጣ ።
በእውነት የቆመው በሰላም ተራራ
ጀግናው ጋዜጠኛ ሳይሰማ ያን ጉራ
ፍጹም ንቅንቅ ሳይል ከቆመበት ስፍራ
መልእክቱን ሲያሰማ ሆኖ የሱ ተራ።
”በአንባ ገነን ስርአት አንገታችን ታንቆ
አንድ ህዝብ በማፍረስ ዜግነትን ንቆ
መብት እየረገጠ ጎስነት አጥብቆ
አሁን እዚህ ያለው በወገኑ ስቆ
ዛሬ የምለውን ቢሰማኝ አጥብቆ።
ሁሌ ለሰው ልጅ መብት ለነጻነት ሲሉ
ሰላም ተደግፈው ለእውነት ሲታገሉ
በሽብር ተከስሰው ለእስር የተጣሉ
በነቀርሳው ስርአት የታመሙ ሁሉ።
ስለእናንተ መጮህ ስለ ሆነ ወቅቱ
ጊዜ ሳይሰጠው ታርሞ ስህተቱ
ቂም በቀል ተሽሮ ተገልጦ እውነቱ
እርምጃ እንዲወሰድ እናንተን ሊፈቱ
ለአለም መሪዎች ይድረስ መልእክቱ።
ነጻነት ለሰው ልጅ ያ ታላቅ ስጦታ
ሀይማኖት ወይ ጎሳ ከቶ ሳይለይ ጾታ
በአገሬ ስር ሰዶ እንዲሆን አለኝታ
በብርሀን ይነገር ዛሬ ሳይመሽ ማታ።
በአገሬ ያንዣበበው ከባድ የግፍ ጥላ
ውሎ አድሮ ሰንብቶ ከጊዜ በኋላ
በድንገት አንድ ቀን ያ ጽዋ ሲሞላ
መአበሉ ከባድ ነው ፍች የሌለው መላ።
ዛሬ የምትመክሩበት የምግብ አጀንዳ
በአስከፊው ስርአት ዘወትር ለተጎዳ
ነፃነት ሲናፍቅ ወድቆ ረግፎ ሜዳ
ለተቆራኘው ህዝብ መከራና ፍዳ
ምግብ አይሽረውም አይሆነውም ፋይዳ።
ነፃነትን ልድገመው ምንጊዜም ነፃነት
ነፃነት ከሌለ ለሰው ልጆች በውነት
ውርደት ስለሆነ ፍጹም በቁም መሞት
እኛ የተራብነው ተርፎን ሳለ መሬት
አባቶች ባቆዩን አምነን በዜግነት
ሰርተን መኖሩ ነው ኮርተን በነፃነት።
ዛሬም ቢጨልምም በአገሬ ሳይነጋ
የአለምን እርዳታ ሳላሳጣው ዋጋ

በመርከብ በሰፌድ ምግብ ቢዘረጋ
ምትክ አይሆነውም ለነያነት ጸጋ።”
መልእክቴ ይድረሰው ዛሬ ለዚህ ሸንጎ
አንባ ገነን መሪ ለብር አድግድጎ
እዚህ ቢሰለፍም በህዝብ ስም ሰርጎ
ወገኔ የራበው ሲሆን ሰላም በጎ
ዳቦ አይፈውሰውም ነፃነት ፈልጎ።
ከማንም ጠብ የለኝ ፈጽሞ ቅያሜ
መናገር ግዴነው በሚፈቅድ አቅሜ
አገር ቤት ስላሉት ስለእህት ወንድሜ
ዘወትር ስቃያቸው ስለሆነ ህመሜ።”
አነዚህ ቃላቶች አዳራሹን ሞልተው
ለሁሉም ታዩና እንደመብረቅ በርተው
ሰብሰብም በማለት በድምጻቸው ጎልተው
ያንን ታላቅ ሸንጎ ጸጥታውን ነስተው
በንፋስ ታጅበው መልእክት አበርክተው
ከአንድ ሰው እራስ ተያይዘው ገብተው።
በጆሮ አቋርጠው ሰውነት አምሰው
አእምሮ ሲደርሱ ህሊና ቀስቅሰው
ማሰብን ሲጀምር እንደአንድ ተራ ሰው
ከወርቅ መዘኑና ከብደው አስጎንብሰው።
የአገር የህዝብ በደል ስቃዩም ፈተና
መታየት ሲጀምር በሽታው ጸናና
ፍጹም ሳያገግም አንድ ቀን ሳይቀና
ውሎ አድሮ ከርሞ በጣም ስለጠና
መድሀኒት ፍለጋ እሩጫ ተያዘና።
ሀኪሞች ተመርጠው በሙያ የነጠሩ
በጣም የታወቁ ታድነው በአገሩ
ሌት ተቀን ቢደክሙ ለማዳን ቢጥሩ
ሊፈቱት አልቻሉም ተቋጥሮ ነገሩ።
ይህን እንቆቅልሽ የህይወትን ካርታ
እኔ ባላውቀውም ማን እነደሚፈታ፣
ጊዜ ፈቅዶ ስትይዝ የመሪነት ቦታ
አንተሰው እወቀው አስብ በእርጋታ
እጅህ የገባውን የስጣልን ስጦታ
ለሚጠብቅህ ህዝብ በተስፋ በአለኝታ
ቁልፍ መሆንህ ቀርቶ ጋሻና መከታ
ንቀህ ከረገጥከው ወድቆ እንዲንገላታ
የጫንክበት ስቃይ ተከመችቶ ማታ
ሰውነትን ነፍጎህ የመንፈስን ደስታ
በእድሜ ለሚወሰን ለአጭሩ ቆይታ
ያደርግህ ይሆናል ብቸኛ ከርታታ።

አንባቢ እንዳይሰለች ፍጹም ሳልዘነጋ
ትንሽ ጊዜ ቢኖር መልእክቴን ሳልዘጋ፣
እውነትን ተርጓሚ የተነፈግን ዳኛ
ስልጣን መረገጫ ሆኖብን ቁራኛ
መጠጊያ የለሽ ዜጋ ከርታታ ብቸኛ
ነፃነት የተራብን የመብትም ጥመኛ
ሆነን ለምንጮኸው የስቃይ ጓደኛ
ለመሰል ወገንህ ለጭቁኖች ለኛ
የአገር የህዝብ ልጅ አበበ አንደኛ
መሆንህ ይታወቅ ጀግናው (ታላቅ) ጋዜጠኛ።

.______///_______.
ተስፋዬ ዘርፉ።